# <u>አስመራ ደርሶ መልስ</u>

ወንድሙን አርዶበት ፤ ቤቱን አፍርሶበት ... ያለፈው ሳይበቃ
ስራውን አረስቶ ፤ ጆሮ ዳባ ካለ ... ታጥቦ ፤ ሲሆን ጭቃ
እንደ ማሞ ቂሎ ፤ በነደፈው እባብ ... ድጋሚ ሲጠቃ
ሲነግሩት ካልሰማ ፤ ቅዠት ፤ እውን ላይሆን ... ከእንቅልፉ ካልነቃ
በአይን የሚታየው ፤ በጅ የሚዳሰሰው ... ለትምህርት ካልበቃ
እሱው ባመቻቸው ፤ እሱው በጠረገው ... አውድማ ቢወቃ
ማን ገላጋይ ይሁን ፣ ወዶ ለገባበት ... ማን ፣ ይሁን ጠበቃ?
ማዘን ያስቸግራል ፤ እራሱን አዋርዶ ... ፈቅዶ ፤ ለሆነ እቃ ።

ለአስራ ሰባት ዓመት ፤ ቀፍቅፎ ያሳደገው ... ጡጦውን አጥብቶ
ሀሁ ያስቆጠረው ፣ በግንጠላ ክህነት ... እስካፍንጫው ግቶ
አገር እንዲበትን ፤ በዘር በጥላቻ ... እንደ ፈረስ ፣ ገርቶ
ይረዳኛል ብሎ ፤ ወደሱ መገስገስ ... መሳሪያን አንግቶ
ባገር ከተጠላ ፤ ከውሻ ለመዳን ... ተኩላ ፤ ጉያ ገብቶ
ተቀባይ ሳይጠፋ ፣ የከፋው ባላገር ... ካፅናፍ ፤ አፅናፍ ሞልቶ
ቢታመሙ አስታሞ ፣ መንገድ የሚመራ ... አብልቶ አጠጥቶ
መሄጃ ያ ሳይቸግር ፣ ጫካው ተረተሩ ... ሳለ ፣ ደፋር አጥቶ
እራስን ማዋረድ ፤ እራስን ማስጠቃት ... ለጠላት ፣ እጅ ሰጥቶ
ሳይተኩሱ መውደቅ ፣ ወዶ ፤ ገብቶ ማለቅ ... ምን ይሉታል ፤ ከቶ ?

ባወቅኩሽ አወቅኩህ ፤ በወንዜ ጓደኛ ... የተመራረጡ
ካውሮፓ አሜሪካ ፤ ካሜሪካ አስመራ ... ቀን ከሌት ፣ ሲሮጡ
ተስፋ እየቀለቡ ፤ ምንም ላይፈይዱ ... ምንም ላያመጡ
አሁንም ክፍፍል ፤ አሁንም ፣ ጎጥ መንደር ... ሲሉን ሲያስደምጡ
ሸርሸር አርገውት ፤ አስመራ ፣ ደርሶ መልስ ... ትኬት ማስቆረጡ
በህዝብ ሰቆቃ ፤ በትግል መቀለድ ... በዛ ማላገጡ
ባይወስዱን ምናለ ፤ ከድጡ ወደ ማጡ ?
ዛሬ ነገ ፤ ሳይሉ ፤ ከሚያደፈርሱት ... ከሚበጠብጡ
የማያውቁበትን ፤ አርፈው ቢቀመጡ ... ከትግል ቢወጡ ።

ታዛቢው ... December 22, 2010